ኢየሱስ መሲሕ፡ ተንሥአ እሙታን!
በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን!
ዐሠሮ ለሰይጣን! አግዓዞ ለአዳም!
እምይእዜሰ፡ ኮነ፡ ፍሥሓ ወሰላም!
በኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ ዘለዓለም!

ኢየሱስ መሲሕ፡ በታላቅ ኃይልና ሥልጣን!
ተለይቶ ተነሣ፡ ከመቃብረ ሙታን!
ሰይጣንን አሠረው! አዳምንም ነጻ አወጣው!
ከዛሬ ጀምሮ፡ ኾነ፡ ደስታና ሰላም!
በኢትዮጵያ፡ መንግሥተ-እግዚአብሔር፡ ለዘለዓለም!

ይድረስ፡- ለኪዳናዊ ወንድሜ ግርምሽ።

በሰላም፣ በተድላና በጤና የሚያኖረን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይኹን!

እያደረክ ያለውን እጅግ በጣም ጥበብ የተሞላበት አካኼድ፡ ማድነቅ እፈልጋለሁ።

እንግዲህ፡ በዚህ፡ አንተ እየፈጠርክ ባለው መልካም መድረክ፡ "ብዙ ሰዎች፡ ወደመልካምቹ የዕውቀት መጻሕፍት ይደርሳሉ!" የሚል እምነት አለኝ።

ቴዲ አፍሮም፡ በራሱ በኩል፣ በሕይወቱም፣ በዘፈን ሥራዎቹም፣ በሚያደርጋቸው ቃለ-መጠይቆችም ውስጥ፡ ይህንኑ እያደረገ እንዳለ በቀላሉ መረዳት እንችላለን። እኔ ራሴ የሰማሁት ባይኾንም፡ በቀደመው የዘፈን ሸክላው [Album ሥራው] ላይ፡ ቃለ-መጠይቅ ሲደረግለት፡ የጋሼን [የንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስን] ስም በይፋ ማንሣቱንና መጥቀሱን የሰሙ ሰዎች ነግረውኛል።

ይህ ያለንበት ጊዜ፡ ክፉነት፣ ምንም (አልቦ) ከኾነው ህልውናው ተነሥቶ፡ ሕይወት ያለው መስሎ፡ ታይቶና ተገኝቶ፡ ዘላለማዊ ህልውናና ሕይወት ያለው ኾኖ የሚገኘውን መልካምነትን፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ የተገዳደረበት ጊዜ እንደመኾኑ፡ መልካምነት ታላቅ ፈተና ውስጥ የገባችበት ጊዜ ነው። ክፉነት፡ ከአልቦነቱ ተነሥቶ፡ ሕይወት ያለው ኾኖ የተገኘው፡ እኛ ሰዎች በባለማወቅ፡ ትብትብ ውስጥ ስለተገኘን ነው። ልክ እውነትን ባወቅን ጊዜ ግን፡ ክፉነት ሕይወት ያጣል፣ ወዳለመኖሩ ይመለሳል። ስለዚህ፡ የክፉው ወገን መሥራችና ጉዳይ አስፈጻሚ የኾኑ አካላት፡ ተግተው የሚሠሩት፡ ሰዎች ኹልጊዜም ቢኾን በባለማውቅ ህልውና ውስጥ እንዲገኙ ለማድረግ ነው።

ይህ አንተ አሁን እያሠራኽ ያለኸው ሥራ፡ ሰዎችን፡ በቀላሉ፡ የመልካሙ ዕውቀት ምንጭ ወደኾነው፡ ወደ ጋሼ መጻሕፍት የሚያመጣ በመኾኑ፡ የክፉውን ወገን በማሸነፍ ረገድ ታላቅ ድርሻ አለው። "አካኼዱም፡ ጥበብን የተሞላ ነው!" ያልኩት ለዚህ ነው።

ኪዳናዊ ወንድምህና የክህነት ባልደረባህ፡- ዮሓንስ ደጉ።